# የቆሎ ተማሪ የትምህርት ቤት ሕይወት፥ በፍኖተ ሰላም አካባቢ ማሳያነት

የኔአሳብ የሥራህ[1]

**Abstract**

The EOTC school system is believed to be originated in the Aksumite Kingdom in the first century with the introduction of Christianity. In the course of the centuries, the school system has grown and changed in many ways. With the expansion of the Kingdom and Christianity to the south and southwest parts of he country, churches and monasteries were founded, which became for centuries important centers of learning. In their present form, the church schools evolved during the “golden age” from the 13th to the 16th centuries when the literature of the Church had reached its peak. The schools have in this period confined their educational activities to glorifying the products of past centuries and conveying these to the coming generation. However, the researcher shall not discuss here the historical development, but rather the educational activities of these traditional and indigenous schools. Hence, the objective of this study was to explore the unique life experiences of church students and their folkloric routines as well as different educational practices by taking Finote Selam area as a case study. Data were collected from both primary and secondary sources. The main data collecting methods were ethnographic observations and deep-interviews. The study was conducted based on two months’ ethnographic fieldwork in Finote Selam areas. As observed in the study, yek’olo temariwoch have limited contact with their parents because it was traditionally believed that it could interrupt their daily rehearsal practices if they went back home regularily. As the findings showed, beyond subsistence, begging has a traditionally transmitted belief that the children’s understanding will be escalated if they loss their comfort zone and exposed to harsh situations like begging. Begging here was seen as an activity that instills religious discipline and spiritual development. Their routine lives, as observed in the study, have been full of folkloric beliefs and practices which made students as unique folkgroup.

**Key Words -** Yekolo temari, folk beliefs, begging, creativity, education.

[1] የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ፣ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የትምህርት ዘርፍ የሁለተኛ ዲግሪ አላቸው፡፡ ይህ ጽሑፍ በወቅቱ (በ፳፻፬ ዓ.ም.) አጥኚው የማስተርስ ዲግሪያቸውን ለማግኘት ካቀረቡት የምርምር ሥራ የተቀነጨበና ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥናት መጽሔት (JECS) በሚስማማ መልኩ ታርሞና ተስተካክሎ የቀረበ ነው፡፡ በርግጥ ጥናቱ ከአሥራ ሁለት ዓመት በፊት የተደረገ ቢሆንም፣ ጉዳዩን በዚህ ጊዜ ማንሳቱ ፋይዳውን የሚያሳንስበት አይመስለኝም፡፡ አንድም አሁን በአካባቢው ያለው የቆሎ ተማሪ የትምህርት ቤት ሕይወት በይዘትም ይሁን በቅርጽ ለውጥ ያሳየ ባለመሆኑ፣ አንድም አስተምህሮቱና የትምህርቱ ሂደትና ሥርዓት የተለወጠና የሚለወጥ ባለመሆኑ ጉዳዩን አሁን ማቅረቡ ሩቅ አያስብለውም፡፡ ነገር ግን በእነዚህ አሥራ ሁለት ዓመታት ውስጥ በዘርፉ የተሠሩ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ፈልጎ መከለስ አለመቻሉ የራሱን ክፍተት መፍጠሩ የማይካድ እውነታ ነው፡፡

## ፩. መግቢያ

"የቆሎ ተማሪ የትምህርት ቤት ሕይወት፡ በፍኖተ ሰላም[2] አካባቢ ማሳያነት" በሚል ርእስ የቀረበው፣ የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ አድርጎ የተነሣው የቆሎ ተማሪዎችን የትምህርት ቤት ሕይወት ማሳየት ነው። ጥናቱ ከዚህ አጠቃላይ ዓላማ የሚቀዱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት። እነዚህም የቆሎ ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው ርቀው የሚያደርጉትን ጉዞ ትርጉምና አንድምታ መግለጽ፤ የቆሎ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቆይታቸው ስማቸውን ለምን እንደሚቀይሩ መመርመር፤ እንዲሁም ማኅበረሰቡ ለቆሎ ተማሪዎች ልመናና ደጅ ጥናት ያለውን አመለካከትና የሚሰጠውን ምላሽ መፈተሽ የሚሉ ናቸው። ማንኛውም ጥናት ይዞት የተነሣው ዓላማ ይሳካ ዘንድ የራሱ የሆነ የጥናት ወሰን ይኖረዋል። ይህ ጥናትም ከቦታ አንጻር በጎጃም፣ ፍኖተ ሰላም አካባቢ ብቻ በሚገኙ የቆሎ ትምህርት ቤቶች ላይ ተወስኗል። በጥናቱም ሁለት የቅኔ ቤት ጉባኤዎች፣ አንድ የዜማ ቤት ጉባኤና አንድ የንባብ ቤት ጉባኤ በናሙናነት ተወስደዋል። ከቆሎ ተማሪዎች የትምህርት ደረጃዎች መካከል በንባብ ቤት፣ በዜማ ቤትና በቅኔ ቤት ብቻ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት ነው። ጥናቱ የመጻሕፍት ቤት ተማሪዎችን አይመለከትም።

የጥናቱ ዋነኛ የምርምር ንድፍ ዓይነታዊ ዘዴ ሲሆን፣ በእርሱ ሥር የሚገኘውን ገላጭ የምርምር ስልትን ተጠቅሟል። በመስክ ጊዜ የተሰበሰቡ መረጃዎችን መሠረት በማድረግም የይዘት ትንተና እና ትርጎማ እንደ አስፈላጊነቱ ጥቅም ላይ ውለዋል። በፎክሎር ጥናት መረጃን ከመስክ ለመሰብሰብ የሚረዱ የተለያዩ ዘዴዎች አሉ። ከእነዚህም መካከል ምልከታና ቃለ መጠይቅ ዋና ዋናዎቹ ዘዴዎች ናቸው (ፈቃደ፣ ፲፱፻፺፩):: በዚህ ጥናት ምልከታና ቃለ መጠይቅ የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ናቸው። በእነዚህ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች በፎቶና በድምፅ ማስረጃዎች ተደግፈው ቀርበዋል። በዚህ ጥናት መረጃዎች ከተለያዩ ምንጮች ተሰብስበዋል። ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት ያገለገሉ ሁለት ናቸው። የመጀመሪያው ከመስክ ሥራ በፊት የተለያዩ መዛግብትን በማገላበጥ የተገኘ መረጃ ነው። በዚህ መሠረት ስለፎክሎርና ስለቆሎ ተማሪዎች የተጻፉ መጻሕፍት፣ የዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች፣ የጉባኤ ኀትመቶችና ጥናታዊ ጽሑፎች ወዘተ. በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል። መረጃዎችን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ በሚገኙ የኬኔዲ፣ የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ቤተ መጻሕፍት እንዲሁም በያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤትና በማኅበረ ቅዱሳን ቤተ መጻሕፍት ተሰብስበዋል። ሁለተኛው የመረጃ ምንጭ በመስክ ሥራ ሂደት የተገኘ የምልከታ መረጃ ነው። በዚህ ጥናት ምልከታ የተመረጠበት ምክንያት የተማሪዎችን የዕለት ከዕለት ክንውን በቀጥታ በማየትና በመስማት በመረጃ

መሣሪያዎች ለመሰብሰብ ታስቦ ነው። ምክንያቱም ምልከታ የሚጠቅመው ለጥናት በተመረጠው ቦታ በቀጥታ በመገኘት መረጃዎችን በተለያየ መልኩ ለመሰብሰብ ነውና (Goldstin, 1964, p.77)።

በዚህ ጥናት ተማሪዎች በሚኖሩባቸው ጎጆዎች፣ የመማሪያ ጉባኤዎች፣ የቆጠራ ስፍራዎች ወዘተ. ላይ በመገኘት መረጃዎችን ከምንጫቸው ለመሰብሰብ ተሞክሯል። ቃለ መጠይቅ ሰዎች ስለሚያውቋቸው የተለያዩ ጉዳዮች ጥያቄዎችን በአካል ቀርቦ በመጠየቅ መረጃ ከምንጩ የሚገኝበት መንገድ ነው። ፈቃደ (፲፱፻፺፩) እንዳለው፣ ዝግ እና ክፍት ጥያቄዎችን በመጠየቅ መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል። ለቃለ መጠይቁ የተዘጋጁ ጥያቄዎች የተዋቀሩ እና እንደሁኔታው የተጠየቁ ናቸው። በመስክ ሥራውም በዋናነት መሪ ጌታዎች፣ የቆሎ ተማሪዎች፣ የቤት እመቤቶችና የዕድሜ ባለጸጋ አዛውንቶች ቁልፍ መረጃ አቀባዮች በመሆን አገልግለዋል። እንዲሁም የሀገረ ስብከት ኃላፊዎች እና የመንግሥት ወረዳ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች ተጨማሪ መረጃዎችን በመስጠት አገልግለዋል። እነዚህ መረጃ አቀባዮች የተመረጡት ለጉዳዩ ባላቸው ቅርበትና በአካባቢው ማኅበረሰብ ካላቸው ተቀባይነት በመነሣት ነው። ከእነዚህ መካከል ሦስት መሪ ጌታዎች (መምህሮች)፣ አምስት ተማሪዎች፣ አንድ የቤት እመቤት፣ አንድ የዕድሜ ባለጸጋ አዛውንት በአጠቃላይ ዐሥር ሰዎች ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች በጥናቱ ተሳትፈዋል።

## ፪. ስለቆሎ ተማሪ (ነት) አንዳንድ ነጥቦች

ኢትዮጵያ በ፫፻፴ ዓ.ም. ክርስትናን ከተቀበለችበት ጊዜ ጀምሮ ሃይማኖታዊ ትምህርትን በልዩ ልዩ መንገድ ስትሰጥ ቆይታለች (Ephraim, 2010, p.70)። አገሪቱ ከኦሪት እምነት ወደ ክርስትና ከመሸጋገሯ ጋር ተያይዞ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሊቃውንትን ለማፍራት ሃይማኖታዊ ትምህርት በሰፊው ይሰጥ ነበር (Pankhurst, 1966, p.27)። ብዙውን ጊዜ ሃይማኖታዊ ትምህርት ይሰጥ የነበረው በቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂነት ነው። ከክርስትና ሃይማኖት መስፋፋት ጋር በተያያዘም በተለያየ መልኩ በተለይም ለወጣቶች በይዘቱ ሰፋ ያለ እና በአቀራረቡ የጠነከረ ትምህርት ይሰጥ ነበር (ሀብተ ማርያም፣ ፲፱፻፷፫፣ ገጽ ፵፪)።

ይህንን ሃይማኖታዊ ትምህርት ከሚከታተሉት ወጣቶች መካከል በተለምዶ የቆሎ ተማሪዎች ተብለው የሚታወቁት ቀዳሚ ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህ ተማሪዎች በተለያዩ ስያሜዎች ይጠራሉ። ከእነዚህም መካከል <<የአብነት ተማሪዎች፣>>

<<የቄስ ተማሪዎች>> እና <<የቆሎ ተማሪዎች>> የሚሉት ይጠቀሳሉ። ነገር ግን ለዚህ ጥናት <<የቆሎ ተማሪዎች>> የሚለው ስያሜ ተመራጭ ሆኗል። ሁለቱ ስያሜዎች ያልተመረጡበትን ምክንያት ስንመለከት "የአብነት ተማሪዎች" የሚለው መጠሪያ በዚህ ጥናት ያልተመረጠበት ምክንያት የዚህ ጥናት ተተኳሪ ተማሪዎች በሚገኙበት አካባቢ ያልተለመደ በመሆኑ ነው። ይህ መጠሪያ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል ባዘጋጀው መዝገበ ቃላት <<አብነት>> የሚለውን ቃል ምሳሌ፣ አርአያ ብሎ ከፈታው በኋላ፣ የጠለቀ ትምህርት ያለው እና እውቅ መምህር በማለት ይተረጉመዋል። ይህ ስያሜ አንድም የትምህርት መጀመሪያ መሆናቸውን ለመጠቆምና በሌላ በኩል በእውቀት የበለጸጉ መሆናቸውን ለመጠቆም የተሰጠ ስያሜ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ነገር ግን ስያሜው በተለይም ይህ ጥናት በተካሄደበት አካባቢ የተለመደ ባለመሆኑ በመደበኛነት አገልግሎት ላይ ሲውል አይታይም። በሌላ በኩል ደግሞ፣ <<የቄስ ተማሪዎች>> የሚለውን ስያሜ ስንመለከት ስያሜውን ያገኙት ከትምህርት በኋላ ከሚሰማሩበት ሙያ በአንዱ ላይ ብቻ በመመሥረት ነው። ስያሜው የተማሪዎችን ማንነት ሙሉ በሙሉ አይገልጽም። ምክንያቱም <<ቄስ>> የሚለው ቃል <<ቀሰ>> አገለገለ ከሚለው የግእዝ ግስ የመጣ መሆኑን ኪዳነ ማርያም (፲፱፻፹፣ ገጽ ፹፩) ይገልጻሉ። ስለዚህ ይህ ስያሜ ተማሪዎች ከትምህርት በኋላ በሚሰጡት አገልግሎት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የተማሪዎች ጥቅል መጠሪያ ሊሆን አልቻለም።

<<የቆሎ ተማሪ>> የሚለው መጠሪያ በሁለት ምክንያቶች በዚህ ጥናት ለተማሪዎች መጠሪያ ሆኖ ተመርጧል። በመጀመሪያ ይህ ጥናት የፎክሎር ጥናት እንደመሆኑ መጠን ለአካባቢያዊ ስያሜ ትልቅ ድርሻ ይሰጣል። ለጥናት በተመረጠው አካባቢ ከሁለቱ ስያሜዎች ይልቅ "የቆሎ ተማሪ" የሚለው መጠሪያ በስፋት ጥቅም ላይ ይውላል። እንዲሁም ተማሪዎች ራሳቸውን የሚጠሩበት መጠሪያ ስለሆነ ሊመረጥ ችሏል። በሌላ በኩል ስያሜው የተማሪዎችን ትክክለኛ ሕይወት የሚያሳይ በመሆኑ ነው። በኢትዮጵያ ቋንቋንዎች ጥናትና ምርምር ማእከል በተዘጋጀው *የአማርኛ መዝገበ ቃላት* (፲፱፻፺፪፣ ገጽ ፪፻፫) መሠረት <<የቆሎ ተማሪ ማለት ከየመንደሩ የሚያገኘውን ቁራሽ እንጀራ እንዲሁም ጥራጥሬውን በቆሎ መልክ እያዘጋጀ በመመገብ እንደ ንባብ፣ ዜማ፣ ቅኔ… ወዘተ. ያሉትን የትምህርት ዓይነቶች የሚቀጽል የቤተ ክህነት ተማሪ ነው። >> በዚህ ስያሜ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የሚገኙ ተማሪዎች ጥቅል መጠሪያ መሆኑ እና ስያሜውም የትምህርት ቤት ሕይወታቸውን የሚገልፅ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ኪዳነ ማርያም (፲፱፻፹፣ ገጽ ፯) እንዲሁም <<ጥንታዊ የቆሎ ተማሪ>> በሚለው መጽሐፉ የቆሎ ተማሪ ማለት ጥሬ ቆርጥሞ፣ ውሃ ጠጥቶ በችግርና በረኃብ የሚማር መሆኑን ገልጿል። ከላይ የተነሡት ሁለቱም

ስያሜዎች እንደገለጹት የቆሎ ተማሪ የሚለው መጠሪያ ሕይወታቸውን መሠረት አድርጎ የተሰጠ መጠሪያ ነው። በእነዚህ ምክንያቶች ስያሜው ለዚህ ጥናት የተማሪዎች ጥቅል መጠሪያ ስያሜ በመሆን አገልግሏል።

የቆሎ ተማሪዎች ለቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ለመሆን በቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት መምህር ተዘጋጅቶላቸው የሚማሩ ናቸው። እንደ Pankhurst (1966, p.28) ያሉ ተመራማሪዎች በኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መቼ እና የት ጉባኤ ዘርግተው ማስተማር እንደጀመሩ በውል እንደማይታወቅ ጠቅሰው እንዲያውም ፲፱ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ግን በተደራጀ መልኩ በየቤተ ክርስቲያኑ የተጠናከረ ትምህርት ይሰጥ እንደነበር ለመሞገት ይሞክራሉ። ነገር ግን ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ጉባኤ ተዘርግቶ ትምህርቱ በመደበኛነት በሥርዓት ይሰጥ እንደነበር በዘርፉ ጥናት ያደረጉ አንዳንድ (ለምሳሌ የዳንኤል ክብረትን አራቱ ሃያላንን ማየት ይቻላል) ታሪክ ጠቅሰው ያስረዳሉ። የቆሎ ተማሪዎች ይህንን ሃይማኖታዊ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ተሰባስበው ሲከታተሉ የራሳቸው የሆነ የትምህርት ሥርዓት፣ የአኗኗር ብልሃትና የሕይወት መገለጫዎች አሏቸው። የትምህርት ሥርዐታቸውም በአራት ዋና ዋና ምዕራፎች የተከፈለነው። የንባብ ቤት፣ የዜማ ቤት፣ የቅኔ ቤትና የመጽሐፍ ቤት በመባል ይታወቃሉ። በሌላ በኩል በትምህርት ቤት ሕይወታቸው የእኛ የሚሏቸውና ከቀሪው ማኅበረሰብ ጋር የሚጋሯቸው የሕይወት መገለጫዎች አሏቸው። ይህ ጥናት የቆሎ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ሕይወት ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ነው፥

የቆሎ ተማሪዎች የራሳቸው የሆነ የአኗኗር ሥርዐት አላቸው። ሀብተማርያም (፲፱፻፷፫፣ ገጽ ፪፻፹፰) *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት* በሚለው መጽሐፉ በሀገራችን የሚገኙ የቆሎ ተማሪዎች ሕይወት የራሱ የሆነ ወግና ሥርዐት እንዳለው ገልጿል። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ይህንን ሐሳብ ለማጠናከር Pankhurst (1966, p.30) “In the Christian part of Abysiniya, there is a church in almost every village, every church has its school which is an honored institution. Church schools nearly always in the precincts the church generally with in the outer wall of the church green” በሚል ያቀረበውን ሐሳብ ማየት ተገቢ ይሆናል። በገጠሯ ኢትዮጵያ በእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ የራሱ ቤተ ክርስቲያንና ትምህርት ቤት አለው። ትምህርት ቤቶቹም ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን አቅራቢ የሚሠሩ ናቸው። ኑሯቸውንም የሚመሩት በቤተ ክርስቲያን አቅራቢያና በመምህራቸው ቤት ዙሪያ በኅብረት በሚቀልሷቸው ጎጆዎች ውስጥ ነው። የቆሎ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቆይታቸው የሚያልፉባቸው አራት ዋና ዋና የትምህርት ደረጃዎች አሉ። እነሱም ንባብ ቤት፣ ዜማ ቤት፣ ቅኔ ቤትና መጻሕፍት ቤት ናቸው (ሀብተ ማርያም፣ ፲፱፻፷፫፣ ገጽ ፴፱ እና Pankhurst;

1966, pp.32-33)። እነዚህ ምሁራን እንደሚሉት፣ እያንዳንዳቸው በውስጣቸው ብዙ ንኡሳን ክፍሎች ቢኖሯቸውም አራቱ ደረጃዎች ግን ጎልተው የሚታወቁት ናቸው። እያንዳንዱ ትምህርት የተለያየ መልክ ስላለው በተለይም የትምህርት አሰጣጡ እራሱን ችሎ ሊጠና እንደሚችል ሀብተ ማርያም ይገልጻሉ።

ተማሪዎች ሃይማኖታዊ ትምህርትን ዋና ዓላማ አድርገው ቢነሡም በትምህርት ቤት ቆይታቸው እንደ ታሪክ፣ ግጥም፣ ዜማ፣ ፍልስፍናና መድኃኒት ቀመማ ወዘተ. የመሳሰሉትን የትምህርት ዓይነቶች እንደሚማሩ Pankhurst (1966, p.28) ያስረዳል። ዛሬ ላይ የዘመናዊ ትምህርት ትኩረት የሆኑት የትምህርት ዘርፎች ቀደም ብሎም በኢትዮጵያ የቆሎ ትምህርት ቤቶች ይሰጡ ነበር። በተጨማሪም እነዚህ ትምህርት ቤቶች በሀገራችን ለሚሰጠው ዘመናዊ ትምህርት መሠረት መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል።Pankhurst (ibid, p.29) እነዚህን ተማሪዎች የሚያስተምሯቸውን መምህራን የእውቀት ደረጃና ብስልት ሲገልጽ በአውሮፓ "ፕሮፌሰር" ከሚባሉትና በእውቀት ከበለጸጉት ምሁራን ጋር ሊስተካከሉ እንደሚችሉ ይናገራሉ።

## ፫. የቆሎ ተማሪዎች ሕይወት ፎክሎራዊ (ትውፊታዊ) ገጽታ

ፎክሎር የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ Willam John Thoms በ1846 እ.ኤ.አ. ከተጠቀመበት በኋላ የተለያዩ ምሁራን እንደየዘመኑ የእውቀት ደረጃ የተለያየ ብያኔ ሲሰጡት ቆይተዋል። ሁሉም ስለፎክሎር ብያኔ የሰጡ ምሁራን ፎክሎር የሚለው ጽንሰ ሐሳብ ለብያኔ አስቸጋሪ መሆኑን ሳይጠቁሙ አላለፉም። ጽንሰ ሐሳቡን በቃል መሰየም ብቻ ሳይሆን በውስጡ የሚያጠቃልላቸው ነገሮች ብዛት ጉዳዩን የበለጠ አወሳስቦታል። በተለይም ፎክሎር አንድ የጥናት ዘርፍ መሆኑ እና በተጨማሪም ዘርፉ የሚያጠናቸው ጉዳዮች ጥቅል መጠሪያ መሆኑ ቁርጥ ያለ ብያኔ እንዳይሰጠው አድርጓል (Martha and Martine; 2005, p.1)። ፎክሎር አንድ የእውቀት ዘርፍ መሆኑ፣ የእውቀት ማስተላለፊያ መንገድ መሆኑ እና ፎክሎር በራሱ እንደ አንድ የጥበብ ዘርፍ መቆጠሩ ቁርጥ ያለ ብያኔ ለመስጠት እንዳስቸገረ ገልጿል።በሌላ በኩል ፎክሎር ምንም ይበል ምንም የሰው ልጆችን የዕለት ከዕለት ሕይወት ለሚመለከት ከሰው ልጆች እድገትና ሥልጣኔ ጋር አብሮ እየተለወጠ እንደመጣ መረዳት ይቻላል።

በቅርብ ጊዜ የተሰጡትን የፎክሎር ብያኔዎች ብንመለከት ፎክሎር ትምህርት ቤት ገብተን የማንማረው ነገር ግን መደበኛ ባልሆነ መልኩ ስለራሳችን፣ ከሰዎች ጋር ስላለን ግንኙነት፣ ስለእምነታችን፣ስለባህላችን በአጠቃላይ ስለዓለም ያለንን ግንዛቤ የምንገልጽበት የሕይወታችን ክፍል ነው። Martha እና Martine (ibid p.19) Dndesን በመጥቀስ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የጋራችን የሚሉት ነገር ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ራሳቸውን ችለው ሊጠኑ እንደሚችሉ ይጠቁማሉ። ስለዚህ

የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑት የቆሎ ተማሪዎች እንደ አንድ የኅብረተሰብ ክፍል (group) ተቆጥረው የራሳችን የሚሉትን የሕይወት ዘይቤና የኑሮ ፍልስፍና (ፎክሎር) ማጥናት ይቻላል።

በፎክሎር ጥናት፣ ቡድን (group) የሚለው ጽንሰ ሐሳብ ለአንድ የፎክሎር ተመራማሪ ዋና ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ከላይ ከተሰጠው ብያኔ በመነሣት ፎክሎር ትርጉም ሊኖረው የሚችለው የግድ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ያለው ሚና ሲመረመር በመሆኑ ነው። Ben- Amos (1971, p.14) “folklore is not thought as existing without or a part from a structured group” ብሎ እንደገለጸው፣ ፎክሎርን ከቡድን ነጥሎ ማየት አይቻልም። ምክንያቱም አንድ የኅብረተሰብ ክፍል የራሱን ሕይወት የሚገልጽበትና በሌሎች ዘንድ የሚታወቅበት ልዩ የጋራ ጉዳይ ይኖረዋል። ይህ የጋራ ጉዳይ፣ የእርስ በእርስ ግንኙነት፣ ስለራሳቸው ብሎም ስለሌላው ማኅበረሰብ ያላቸው አመለካካት የሚገልጽበት ደግሞ ፎክሎር ነው። ፎክሎር የአንድን ነጠላ ቡድን ሕይወት ያሳያል ብለን ስንነሣ የጋራ መገለጫ የሆነ ባህል አላቸው ከሚል ሐሳብ ነው። የጋራ የሆነ የሚታወቁበት ባህል ከሌላቸው እንደ አንድ ነጠላ ቡድን ሊቆጠሩ አይችሉም ማለት ነው። ሌላውና ትልቁ ጉዳይ አንድ ነጠላ ቡድን የባህሉ መገለጫ የሆነው ፎክሎር ይጠናል ሲባል የቡድኑ ባህል ከሌሎች የተለየ ነገር ሲኖረው (ተለይቶ የሚታወቅበት ሲሆን) እና ያ ባህል እንዲህ ነው ተብሎ የሚገለጽና የሚተረጎም ሲሆን ነው። በአጠቃላይ አንድን ቡድን ራሱን ችሎ ይጠና ዘንድ ከሌሎች የሚለይበት መገለጫ ሊኖረው ይገባል ወደ ሚል ድምዳሜ ያደርሳል። የቆሎ ተማሪዎችም እንደ አንድ የኅብረተሰብ ክፍል ተቆጥረው ለጥናት ሲመረጡ ከላይ በተነሣው ሐሳብ መነሻነት ነው።

በሌላ በኩል አንድ ቡድን ከላይ የተቀመጡትን ጉዳዮች አሟልቷል ተብሎ ሲጠና ያ ቡድን እራሱን እንዴት ከሌላው ማኅበረሰብ እንደሚለይና ማንነቱን እንዴት ባለ ሁኔታ እንደሚገልጽ መረዳት ይቻላል። በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚመሠረቱ ቡድኖች ራሳቸውን ከሌሎች የሚለዩበትን ድንበር ያበጃሉ። የአንድን ቡድን እምነት የሚያጠና ተመራማሪም እምነቱ ትክክል ነው ወይም ስሕተት ነው ከማለት ተቆጥቦ እምነቱን በሥነ ቃል፣ በልማድ ወይም በቁሳዊ ባህል አማካይነት እንዴት እንደሚገልጹት ማሳየት ይጠበቅበታል። ስለዚህ አንድን ቡድን በማጥናት ያ ቡድን እምነቱን በሦስቱ የፎክሎር ዘርፎች እንዴት እንደሚገልጸው ማወቅ ይቻላል። ስለህገረሰባዊ እምነት ሲነሣ አብሮ የሚመጣው ወግ ማዕረግ የማያ ሂደት ወይም ሽግግር (rites of passage) ነው። ምክንያቱም ወግ ማዕረግ አንዱ የእምነት መገለጫ በመሆኑ ነው። ማንኛውም ቡድን ይሁን ግለሰብ በሕይወቱ የሚያልፍባቸው የሕይወት ደረጃዎች ይኖሩታል። እነዚህ ደረጃዎችም ለቡድኑም ሆነ ለግለሰቡ

የራሳቸው የሆነ ፋይዳ ይኖራቸዋል (Dorsen; 1972, p.159)። ይህ ራሳቸውን የሚገልጹበትና ከሌሎች የሚለዩበት ዘዴ ደግሞ በዕለት ከዕለት ሕይወታቸው ይገለጻል። ሕይወታቸው የሚታወቀውና የሚጠናው ደግሞ በፎክሎር ነው (Georges and Jones, 1995, p.225)። ስለዚህ በአንድ ቡድን ላይ የሚካሄድ ጥናት የዚያን ቡድን ማንነት ያሳያል ማለት ይቻላል። Georges እና Jones ከላይ ባስቀመጡት ሐሳብ መሠረት አንድ ቡድን ራሱን ችሎ ይጠናል ቢባልም ቡድኑ ለብቻው በተለየ ዓለም እስካልተገኘ ድረስ በዙሪያው ካሉ ሰዎች ወይም ቡድኖች ጋር ግንኙነት መፍጠሩ አይቀርም። በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት የቆሎ ተማሪዎች በአንድ ቡድን ሥር ተጠቃለው የሚኖሩ ቢሆኑም የእነሱን ማንነት ለማጥናት ግን ከእርስ በእርስ ግንኙነታቸው ባለፈ ከሌላው ማኅበረሰብ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማጥናት ያስፈልጋል። ስለዚህ የቆሎ ተማሪዎች በሃይማኖታዊ ተቋም ሥር ያሉ እና የሃይማኖቱ ተከታዮች ቢሆኑም እንደተባለው ሃይማኖታቸውን ሳይለቁ በግልም ሆነ በቡድን የሚፈጽሟቸው ሀገረሰባዊ እምነቶች አሏቸው። በዚህ እምነታቸውም እንደቡድን ተለይተው ይታወቃሉ።

## ፬. የመረጃ ትንተና

በዚህ ጥናት በቆሎ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ቆይታ ጊዜ ተደጋግመው የሚከሰቱና የቆሎ ተማሪዎች መገለጫ የሆኑ እንደጉዞ፣ ስም ቅየራ፣ ልመና፣ ለየት ያለ ማኅበራዊ ሕይወት የመሳሰሉ ጉዳዮች ተዳስሰው ቀርበዋል። ከጥናቱ መረዳት እንደተቻለው ተማሪዎች የሚፈጽሟቸው እንደጉዞ፣ ስም ቅየራ፣ልመና ያሉ ጉዳዮች በተማሪዎች ዘንድ ሃይማኖታዊ፣ ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊ ምክንያቶችን የያዙ ናቸው። እንዲሁም ማኅበረሰቡ ለተማሪዎችና ለልመና ያለው አመለካከት ሁለት ዓይነት እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል። በኅብረተሰቡ ዘንድ ተማሪዎች በአዎንታዊም በአሉታዊም መንገድ እንደሚታዩ ማወቅ ተችሏል። ከጥናቱ መረዳት እንደተቻለው በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ ክረምትና ዐቢይ ጾም ሐሳባቸውን ሰብስበው ለመማርና አዲስ ነገር ለመፍጠር ስለሚያግዟቸው በጉጉት የሚጠበቁ የትምህርት ወቅቶች ናቸው። እንዲሁም በተማሪዎች ዘንድ በዕውቀት በልጦ መገኘት በሚማሩበት ትምህርት ቤትም ሆነ በቀሪው ማኅበረሰብ ዘንድ ያላቸውን ደረጃና ቦታ ከፍ እንደሚያደርግ ጥናቱ ያሳያል። ይህንን ጥናት ለማድረግ ያነሣሣኝ ዋነኛ ምክንያት፣ የቆሎ ተማሪና ሕይወቱ፣ የትምህርት ሥርዓቱና ፈጠራዊ ስልቱ ለቤተ ክርስቲያኗም ይሁን ለአገሪቱ ያደረገው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ሆኖ ሳለ በተመራማሪዎች ዘንድ የሚገባውን ያህል ትኩረት አለማግኘቱ ነው። እንዲሁም የሚጠቀሰው የቆሎ ተማሪዎችን ሕይወት በሰፊው የዳሰሰ ጥናት አለማግኘቴ ነው። ከዚህ በተጨማሪም በአደግሁበት ፍኖተ ሰላም አካባቢ ለቆሎ ተማሪዎች ቅርበት ስለነበረኝ በትምህርት ቤት ሕይወታቸው

ተደጋግመው ከሚከሰቱ ሁኔታዎች በመነሣት ሕይወታቸው ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ያለኝ ጉጉት ነው።

## ፬.፩ ተሜና የሕይወት ውጣ ውረዱ

በቆሎ ተማሪዎች ሕይወት ውስጥ የሕይወት ውጣ ውረድ ወይም ጉዞ የመጀመሪያው ክስተት ነው። በተማሪዎች ሕይወት ውስጥ ከንባብ ቤት ተማሪዎች በስተቀር በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ያሉ ተማሪዎች በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት አድካሚና እልህ አስጨራሽ ጉዞ ያደርጋሉ። ተማሪዎች የሚያደርጉት ጉዞ ሃይማኖታዊም ሥነ ልቡናዊም ምክንያት አለው። ተማሪዎች ጉዞ ከሚያደርጉባቸው ምክንያቶች መካከል ደጋግመው የሚጠቅሷቸው ከቤተሰቦቹ ጋር በምቾት እየተኖረ ትምህርት አይገባም በሚል እምነት የተነሣ፣ በግብርና ሥራ ሳይጠመዱ ሙሉ ጊዜያቸውን በትምህርት ለማሳለፍና የተሻለ መምህር ፍለጋ የሚሉት ናቸው። ዋነኛው የአባቶች ሐሳብ ግን ተማሪዎች ከቤት ወጥተው፣ ከቤተሰብ ተለይተው የማኅበረሰቡና የኅብረተሰቡ ልጆች ሆነው እንዲያድጉ በማሰብ ነው። ተማሪዎቹ አድገው ለክብር ሲበቁ፣ ዛሬ እነሱን በክብር ያሳደገውንና በአካልም፣ በመንፈስም፣ በሥነ ልቡናም የሚያውቁትን ማኅበረሰብ በክብር እንዲያገለግሉ በማሰብ ነው። ከዚህ በተጨማሪ፣ ተማሪዎቹ ከቦታ ወደቦታ ስለሚሄዱ የልዩ ልዩ ማኅበረሰቦችን ልዩ ልዩ ባህል ስለሚያዳብሩ ነገ ለሚሾሙት ሕዝብ ባዕድ አይሆኑም። የቤት ሥራው ከወዲሁ በብልሃት ተሠርቷልና።

በተማሪዎች ሥነ ልቡና ትምህርት መሥዋዕትነትን፣ መፈተንና መቸገርን ይፈልጋል። በምቾትና በድሎት እየተኖረ ትምህርት አይገባም የሚል ነው። የተሻለ ነገር ለማግኘት ከፍ ብሎ ለመገኘትና ዓላማን ለማሳካት ፈተናዎችን ማለፍና በችግር አለንጋ መገረፍ አለብን ብለው ስለሚያምኑ ቤተሰቦቻቸውን ጥለው ጉዞ ያደርጋሉ። ተማሪዎች ዕውቀት ተርበውና ጥበብን ፈልገው ከቤተሰቦቻቸው ተነጥለው ሲወጡ የሚያደርጉትን ጉዞ ለዓላማ መሳካት የከፈሉት መሥዋዕትነት አድርገው ይቆጥሩታል[3]። በመስክ ቆይታዬ በአራቱም ጉባኤዎች ካሉ ተማሪዎች እንደተረዳሁት፣ ተማሪዎቹ በመንገዳቸው "እመቤታችን ማርያም ከመዓትና ከችግር ታወጣናለች፣ ታዝንልናለች፣ ታበረታታናለች" የሚል የጸና እምነት እንዳላቸው ነው (ሚያዚያ ፴፣ (፳፻፫)። በጉዞ ወቅት የእሷን ስም ጠርተው ከለመኑ ጦም የሚያሳድራቸውም ሆነ ባዶ እጃቸውን የሚሰዳቸው እንደሌለ፤ ጉዟቸውም ሙሉ በሙሉ በአምላክ የሚደገፍና እነሱም ለጉዞ የተመረጡ እንደሆኑ ያምናሉ። ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው ተነጥለው ሲወጡ ዋና ዓላማ አድርገው የሚነሡት ዕውቀትን/ጥበብን እና ጽድቅን ፍለጋ ነው። ይህንን

[3] መረጃ ሰጪ፡- ሙሴ ተሻገር (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ ፳፱፣ ፳፻፫)።

የፈለጉትን ለማግኘትም ከወገን ተነጥለው አስቸጋሪ የሆነውን ጉዞ ይጀምራሉ። አድካሚውን ጉዞ አድርገው የሚፈልጉትን ካገኙ በኋላ ለጊዜው ተሰናብተዋቸው ወደተለዩዋቸው ቤተሰቦቻቸውና ማኅበረሰባቸው ከትልቅ ማዕረግ ጋር ይመለሳሉ።

የቆሎ ተማሪዎችም በትምህርት ቤት ሕይወታቸው የተለያዩ የሕይወት ደረጃዎችን ያልፋሉ። ለትምህርት ቤተሰቦቻቸውን ጥለው ይሰደዳሉ፤ ከስደት መልስም በአካባቢው የተከበሩ የሃይማኖት መሪዎች ይሆናሉ። ይህንን የተማሪዎችን ወግ ማዕረግ በሁለት መልኩ ማየት ይቻላል። አንዱ Marthaና Martine (2005፣ P.110) እንደሚሉት ወግ ማዕረግ/ሽግግር የሚባለው ነገር የግለሰቡ ሕይወት ላይ ትልቅ አሻራ አሳርፎ የሚያልፍ ነው። የቆሎ ተማሪዎች ከተማሪነት፣ ከስደትና ከችግር ወደ መሪነት የሚሸጋገሩበት ደረጃ በሕይወታቸው ትልቁን ቦታ ይይዛል። በሌላ መልኩ የቆሎ ተማሪዎች ወደ ማዕረግ የሚያደርጉት ጉዞ ከሚታዊ ጉዞ ጋር ሊዛመድ ይችላል። ቴዎድሮስ ገብሬ (፲፱፻፩፣ ገጽ ፵፫) እንደገለጸው ማንኛውም ተጋዳሊ ለገድል ሲጠራ የሚያልፍባቸው ሦስት ምዕራፎች አሉ። እነዚህም ከወገን መለየት፣ ወደ ጥብቅ ስፍራ መዝለቅና ከስፍራው አንዳች በረከት ይዞ መመለስ ናቸው።

እነዚህ ምዕራፎች በቆሎ ተማሪዎች ሕይወት ውስጥ ተደጋግመው የሚከሰቱ ሁነቶች ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ይህ የተማሪዎች ጉዞ ራሱን የቻለ የወግማዕረግ ማግኛ ሂደት ተደርጎ ሊቆጠር የሚችል ነው። ምክንያቱም ተማሪዎቹ ጉዞ ከጀመሩበት ደቂቃ ጀምሮ ከነባር ሁኔታ ወደ አዲስ ሁኔታ፣ ከነባር የአኗኗር ዘይቤ ወደሌላ የኑሮ ዘይቤ ይሸጋገራሉና።ከቤተሰቦቻቸው ጥላ ሥር ወጥተው ራሳቸውን ማስተዳደር የሚጀምሩበት ሂደት ነው። በሌላ በኩል እነዚህ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ቆይታቸውንና ከአገር አገር መንከራተታቸውን አጠናቀውና የሚፈልጉትን አግኝተው ወደተነሡበት ማኅበረሰብ ሲመለሱ የሚሰጣቸው ክብርና ኃላፊነት ሌላው የወግማዕረግ መገለጫ ሊሆን ይችላል። ተማሪዎች ከአገር አገር ከመምህር መምህር ተዟዙረው ያገኙትን እውቀት ይዘው ሲመለሱ ማኅበረሰቡ በደስታ ይቀበላቸዋል። ሃይማኖታዊ ተቋማትን እንዲመሩም ኃላፊነት ይሰጣቸዋል። ከዚህ በኋላ ማኅበረሰቡን ከፈጣሪው ጋር የሚያገናኙ፣ የተጣሉትን የሚያስታርቁ፣ በረከት የሚያስገኙ፣ ወዘተ. ይሆናሉ። ይህንን ሁሉ እንዲያደርጉ የሚሰጣቸው ክብር ከጉዞው በኋላ የመጣ ስለሆነ እንደአንድ የሕይወት ሽግግር ይታያል።

## ፬.፪ ተሜና ስም ቅየራው

በቆሎ ተማሪዎች ሕይወት ተደጋግመው ከሚመጡ ክስተቶች መካከል ስም ቅየራ አንዱ ነው። ማንኛውም በቆሎ ትምህርት ቤት የሚገኝ ተማሪ ቤተሰቦቹ ያወጡለትን ስም ቀይሮ

*በሌላ ስም ይጠራል። ከተማሪዎች በተገኘ መረጃ መሠረት ስማቸውን የሚቀይሩበት ብዙ ምክንያቶች አሏቸው። ምክንያቶቹ ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ መሠረት ያላቸው ናቸው። ተማሪዎች ስማቸውን ከሚቀይሩባቸው ምክንያቶች መካከል ከቤተሰብ ለመደበቅ ሲሉ የሚያደርጉት ድርጊት መሆኑ ይጠቀሳል። ይህ ምክንያት ቀደም ብሎ ከተነሣው ከጉዞ ሐሳብ ጋር የተያያዘ ነው። ተማሪዎች ጉዞ ሲያደርጉ ከቤተሰቦቻቸው ፈቃድ እንደማያገኙ ቀደም ብሎ የተጠቀሰውን ማስታወስ ይቻላል።*

*ከተማሪዎች እና ከወላጆች[4] በተገኘ መረጃ፣ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ፈቅደው ቢልኳቸውም የእነሱ ዓላማ በአካባቢያቸው በሚገኙ የንባብ ቤቶች ፊደል እንዲቆጥሩና ዳዊት እንዲደግሙ ነው። ስለዚህ ከዚህ ከፍ ወደሚል ደረጃ ጉዞ የሚያደርግ ተማሪ ከወላጆቹ ፈቃድ አያገኝም። ስለዚህ ጉዞውን የሚያደርገው ከቤተሰቦቹ በመደበቅ ነው። ቤተሰቦቹም የጠፉ ልጃቸውን በየጉባኤው ሰው እየላኩ ማፈላለግ ይይዛሉ። ቤተሰብ ለልጁ ባወጣለት ስም እየጠራ ቢፈልግም ልጁ ገና ወደጉባኤው ሲቀላቀል ስሙን ስለሚቀይር አየሁ የሚለው ሰው አያገኝም። በዚህም ተማሪዎች ስማቸውን ሲቀይሩ ለትምህርታቸው የሚከፍሉት መሥዋዕትነት አንዱ ማሳያ ተደርጎ ይቆጠራል። ለተማሪዎች ስም ቅየራ በምክንያትነት ከሚጠቀሱት መካከል ሃይማኖታዊ ይዘት ነው። ተማሪዎች የስማቸውን መለወጥ ከሃይማኖታቸውና ከሰብዕናቸው መለወጥ ጋር ያያይዙታል። ዓለማዊ ሕይወት ትተው ወደ መንፈሳዊ ሕይወት መግባታቸውን መነሻ በማድረግ ቤተሰብ ያወጣላቸውን ዓለማዊ ስም ይለውጣሉ።በስማቸው መለወጥ ምክንያት ማንነታቸው መለወጡን አምነው ይቀበላሉ። ይህ ከሰብዕና እና ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ ስም ቅየራ መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ይናገራሉ[5]። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮቹን ሲመርጥ ስማቸውን እንደለወጠው ሁሉ እነሱም ለመምህራቸው ራሳቸውን እንደ ደቀመዝሙር ስለሚቆጥሩ ስማቸውን ይለውጣሉ።*

*በሌላ በኩል በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጠቀሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮቹን ሲመርጥ ከሃይማኖታቸው መለወጥ ጋር በተያያዘ ስማቸውን ቀይሯል። ተማሪዎችም ስማቸውን ሲለውጡ እንዲሁ በግምት አይደለም፤የወደፊት ፍላጎታቸውን፣ ምኞታቸውን፣*

---

[4] *መረጃ ሰጪ፦ወ/ሮ ሽታዬ ደለለየቤት እመቤት (ግንቦት ፲፩፣ ፳፻፫)፡፡*

[5] *መረጃ ሰጪ፦ ተማሪ ላእከ ማርያም አንተነህ (ቃለ መጠይቅ ሰኔ ፲፱፣ ፳፻፫))፡፡ ይህ ተማሪ ቤተሰብ ያወጣለትን ስም ባይነግረኝም ነገር ግን የአባቱ ስም አንተነህ ይባላል፡፡ ስሙንም ላእከ ማርያም አንተነህ›› ብሎ ለውጦታል፡፡ ‹‹የማርያም ተማሪ አገልጋይ ነህ›› እንደማለት ነው፡፡ ዋናው ጉዳይ ግን የማርያም መልእክተኛ ወይም አገልጋይ መሆኑን ማስረገጥ ነው፡፡ በዚህም የስም ለውጡ የተማሪውን የዓላማና የተልእኮ ያሳያል፡፡ ስለዚህ ይህ ስያሜ ከተማሪው ሕይወት ጋር የተያያዘ ፍቺ ይሰጣል፡፡ ተማሪዎች የድንግል ማርያምን ስም ጠርቶና እሷን አምኖ የሚኖሩ መሆኑን በስሙ መግለጽ ችሏል፡፡ ብዙዎቹ ተማሪዎች የሚጠሩባቸው ስሞች ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ወይም ደግሞ የጻድቃን ስሞች ናቸው፡፡ ብዙውን ጊዜ ስማቸው በግእዝ ቋንቋ የተሰየመ ነው፡፡ በአጠቃላይ በቆሎ ተማሪዎች ሕይወት ውስጥ ስም ቅየራ አንድ ጊዜ ብቻ የሚከናወን አይደለም፤ ምክንያቱም እንደአስፈላጊነቱ ከትምህርት ቤት ሲዘዋወሩም ስማቸውን አብረው ይለውጣሉ፡ ፡*

አድናቆታቸውን ሁሉ ሊጠቁም በሚችል መልኩ እንጂ። ቆሎ ተማሪዎች ዘንድ ስም ሲቀየር የሚለወጠው ስም በራሱ ወይም ከአባታቸው ስም ጋር ሆኖ አንድ ዓይነት ፍቺ መስጠት አለበት። ይህ ስም ትርጉም እንዲሰጥ አድርጎ መለወጥ ሃይማኖታዊ መሠረት እንዳለው መረዳት ይቻላል። ለዚህም በመጽሐፍ ቅዱስ የሉቃስ ወንጌልን መጥቀሱ ነገሩን የበለጠ ያብራራዋል። <<ሲነጋም ደቀመዛሙርቱን ወደ እሱ ጠራቸው። ከውስጣቸውም ዐሥራ ሁለቱን መረጠ፤ **ሐዋርያት** ብሎም ሰየማቸው" (ሉቃ. ፮÷፲፫)። ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮቹን ጠርቶ ኣላበቃም፤ ይልቁንስ የጋራ መጠሪያ ሰጣቸው። ስለዚህ ይህንን የጋራ ስያሜ ያገኙት የእሱ ተከታዮች ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ነው። ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚከሰት የስም ለውጥም ዝም ብሎ የሚመጣ ሳይሆን ከዓላማና ከተልእኮ አንጻር የሚመጣነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በማርቆስ ወንጌል እንደተገለጸው ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጠው የስም ለውጥ ከአንዳች ፍቺ ጋር የተያያዘ ነው። <<የዘብዴዮስ ልጅ ያዕቆብንና የያዕቆብን ወንድም ዮሐንስንም <<ቦአኔርጌስ>> ብሎ ሰየማቸው፤ ትርጉሙም <<የነጎድጎድ ልጆች>> ማለት ነው (ማርቆስ፣ ፫÷፲፫)። ከላይ ከቀረቡት ሁለት ጥቅሶች መረዳት እንደሚቻለው ስም በግልም በቡድንም ሊለወጥ ይችላል። ነገር ግን ስያሜው ከጠባይ እና ከግብር ጋር የሚዛመድ ነው። ተማሪዎችም ከዚህ ሃይማኖታዊ መሠረት በመነሣት ስማቸውን ሲለውጡ ትርጉሙን በማሰብ ነው።

በአጠቃላይ በቆሎ ተማሪዎች ሕይወት ውስጥ ስም ቅየራ የአንድ ጊዜ ተግባር/ድርጊት ብቻ አይደለም። ተማሪዎች እንደ አስፈላጊነቱ ከትምህርት ቤት፣ ትምህርት ቤት ሲዘዋወሩ ስማቸውን አብረው ይለውጣሉ። አንዳንድ ተማሪዎች በሚማሩበት ጉባኤ ጥፋት ሲገኝባቸውና ከጥፋታቸውም ሳይማሩና ስሕተታቸውን ሳያስተካክሉ ሲቀሩ መምህሩ ለሌሎች ተማሪዎች ደኅንነትና ክብር ሲሉ ከጉባኤው ያሰናብቷቸዋል። ነገር ግን እነዚህ ተሰናባች ተማሪዎች ወደሌላ ጉባኤ ሲቀላቀሉ የኀደፈ ስማቸውን ስም ለውጠው በሌላ ስም ሊገለገሉ ይችላሉ። የስማቸውን በቀየር እንደመደበቂያ (ማምለጫ) ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ይህ ግን ሁሉም ተሰናባች ተማሪ የሚያደርገው ተግባር ነው ወደሚል መደምደሚያ የሚወስድ አይደለም።

## ፬.፫ ተሜና ልመና

ልመና የቆሎ ተማሪዎች ተለይተው የሚታወቁበት ተግባራቸው ነው። የቆሎ ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚያሳልፉትን ሕይወት የሚማሩት <<በእንተ ስማ ለማርያም>>ብለው ለምነው በሚያገኙት ቁራሽ ነው።[6] ልመና በቆሎ ተማሪዎች

[6] የቆሎ ተማሪዎች ለትምህርት ከቤተሰቦቻቸው ርቀው ሲሰደዱ ተስፋ የሚያደርጉት ዓለማዊ ነገር

ዘንድ የራሱ የሆነ ደንብና ሥርዓት አለው። ማንም ተማሪ በፈለገው ሰዓት ወጥቶ መለመን አይችልም። የቆሎ ተማሪዎች ለልመና የሚንቀሳቀሱት በአማካይ ከምሽቱ ፀሥር ሰዓት በኋላ ነው። ይህ የተወሰነ ሰዓትም የቆሎ ተማሪዎች ከሌላው በልመና ከሚተዳደር ሰው ተለይተው እንዲታወቁ ያደርጋቸዋል። ከተማሪዎች በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው፣ የመለመኛ ሰዓታቸው ምሽት ላይ መሆኑ በዋናነት ሁለት ምክንያቶችን የያዘ ነው። የመጀመሪያው ምክንያት ከሚለምኑት ማኅበረሰብ የሥራ ባህል ጋር የተያያዘ ነው። ይህ ጥናት በተካሄደበት አካባቢ በጠዋት ተነሥቶ በየሥራ ተሰማርቶ የሚውለው ገበሬ ወደቤቱ የሚመለሰው ፀሐይ ስታሽቆሎቁል በመሆኑ ነው። ተማሪዎች ከዚያ በፊት ለልመና ቢነሡ በየተመደቡበት መንደር ያለሰው ቤት ዘግቶ ስለሚወጣ ቤት ሊያገኙ የሚችሉት ሕፃናትን ብቻ ነው። ስለዚህ ለልመና ወጥተው ባዶ እጃቸውን እንዳይመለሱ በመፍራት የገበሬዎቹን ወደ ቤት የመመለሻ ሰዓት ጠብቀው ነው የሚንቀሳቀሱት።

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ከተማሪዎች የትምህርት ሥርዓት ጋር የተገናኘ ነው። በቆሎ ተማሪዎች ከሰዓት በፊት ያለው ሰዓት አብዛኛው የትምህርት ሰዓታቸው ነው። ስለዚህ ለልመና የሚነሡት ከትምህርት ሰዓታቸው መጠናቀቅ በኋላ ነው። ለምሳሌ በቅኔ ቤት ያሉ ተማሪዎች በጠዋት ተነሥተው የዕለቱን ቅኔ የሚቆጥሩበት ታሪክ በመምህራቸው ይነገራቸዋል። ይህንን ታሪክ ይዘው በአማካይ ከሦስት ሰዓት እስከ አምስት ሰዓት ለቅኔ ቆጠራ ጸጥ ወዳለቦታ ይሄዳሉ። ከአምስት ሰዓት ጀምሮ በየተራ ለመምህራቸው የቆጠሩትን ቅኔ ይነግራሉ። ስለዚህ ከሰዓት በፊት ያለው ሰዓት ሁልጊዜም በዚህ መንገድ ያልፋል። በመሆኑም ለልመና ከሰዓት በኋላ የሚነሡበት ምክንያት ከግማሽ ቀን በላይ ያለውን ጊዜያቸውን በትምህርት ስለሚያሳልፉ ነው። በመሆኑም ለልመና የሚሰማሩት ይህንን ሁሉ ከፈጸሙ በኋላ በተመሳሳይ ሰዓት ነው።

የለም፡፡ ከቤተሰቦቻቸው ፈቃድ ስለማያገኙ ቤተሰቦቻቸውን አማክረው ስንቅ ከማዘጋጀት ይልቅ በድብቅ አስቸጋሪውን ሕይወት ይጀምራሉ፡፡ Pankhurst እንደሚለው እውቀትን ተጠምቶ የሚሰደድ ተማሪ ብቸኛ ሀብቱ የቁራሽ እንጀራ መለመኛ የምትሆነው “አከፋዳው” ብቻ ናት፡፡ ሕይወቱንም በልመና በሚያገኘው እንጀራ እንደሚመራ ተስፋ በማድረግ ብቻ ነው ቤተሰቦቹን ጥሎ የሚሰደደው (1966፣ p.29) ፡፡ የቆሎ ተማሪዎች እውቀትን ፍለጋ ከቤተሰቦቻቸው ርቀው ከተሰደዱ በኋላ በየትምህርት ቤቱ ሲገናኙ ኑሮአቸው በመተሳሰብ ላይ የተመሠረተ የጋርዮሽ ነው፡፡ ተማሪዎች በጋራ ጎጆ ይቀልሳሉ፤ በጋራ ይሠራሉ፣ በጋራ ይማራሉ እንዲሁም በጋራ ይመገባሉ በማለት ማኅበራዊ ሕይወታቸው የጠነከረ መሆኑን ያስረዳል፡፡



ፎቶግራፍ ፩ - ተማሪዎች ለልመና የመንደር ድልድል ሲያደርጉ

የቆሎ ተማሪዎች በልመና ጊዜ በጥንቃቄ ከሚፈጽሚቸው ሥርዓቶች መካከል የመንደር ድልድል አንዱ ተጠቃሽ ነው። ተማሪዎች በሚማሩበት ጉባኤ ሥር የሚጠቃለሉ የገጠር ቀበሌዎች በሙሉ በዕጣ እየተደለደሉ ለተማሪዎች ይከፋፈላሉ። የመንደር ድልድሉ የሚካሄደው በዕጣ አማካይነት ነው። እያንዳንዱ ለተማሪ በዕጣ በደረሰው መንደር ብቻ ተወስኖ የመለመን ግዴታ ይጣልበታል። ይህንን ድልድል የሚያካሂዱት በጉባኤው የተመረጡ ተማሪዎች ናቸው። ተማሪዎች ለዚህ ኃላፊነት ለመመረጥ በጉባኤው ያሳዩት መልካም ባሕርይ፣ ዕድሜ፣ የእውቀት ደረጃ፣ ሥነ ምግባር ወዘተ. ግንዛቤ ውስጥ ይገባሉ። ይህ ሥርዓት በየሳምንቱ ሁልጊዜ ይካሄዳል። ምክንያቱም እያንዳንዱ ተማሪ በተመደበበት መንደር አንዱ ተጠቃሚ፣ ሌላው ደግሞ ተጎጂ ሊሆን ስለሚችል ድልድሉ በየሳምንቱ እየተቀየረ ሁሉም ተማሪ ሁሉንም መንደሮች የማካለል ዕድል ይኖረዋል። በዚህም አንድ ጊዜ የሄደበት መንደር ላይ ተጠቃሚ ባይሆን በሚቀጥለው ይካሳል ማለት ነው። በዚህ መልኩም ድልድሉን ሚዛናዊ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል።

*ተማሪ ለልመና ሲነሣ ከሚይዛቸው ቁሳቁሶች መካከል ረጅም በትር እና አኮፋዳ ይጠቀሳሉ። ረጅም በትሩ ተማሪው ከውሻ[7] ጋር ግብግብ ሲገጥም ራሱን የሚከላከልበት ብቸኛው መሣሪያው፣ ሲሆን፣ አኮፋዳ ደግሞ ከዘምባባ (በአካባቢው ስያሜ ከጭፉር) የሚሠራ ተማሪዎች የሚለምኑዋቸውን ምግብ ነክ ነገሮች የሚያስቀምጡበት ነው። ነገር ግን አኮፋዳ የሚለምኑትን ነገር ከማስቀመጥ ባለፈ በተማሪዎች ዘንድ ትልቅ ትዕምርት አለው። ድንግል ማርያም ምንጊዜም ለልመና ከወጣ ተማሪ ጋር አብራ መሆኑዋን ማሳያ ጭምር ነው። ተማሪዎችም አጥተን አንመለስም ብለው ያምናሉ። በልመና ያገኙት አነስተኛ/ትንሽ ነገር ቢሆን እንኳ አኮፋዳው ምግቡን ሲነካው ድንግል ማርያም ስለምትባርከው በረድኤት ይበዛል ብለው ያምናሉ። ከዚህ የተነሣም ለልመና ወጥተው ያገኙትን ነገር አኮፋዳቸውን ሳያስነኩ አይመለሱም። ድግስ ወደሚበዛበት አካባቢ እንኳን ሲሄዱ ሁለት አኮፋዳ ይዘው ነው። የለመኑት ነገር ከአኮፋዳው የመያዝ ዓቅም በላይ ከሆነ ትተውት ይመጣሉ እንጂ በሌላ ነገር አይዙትም። ምክንያቱም አኮፋዳ ካልነካው የለመኑት ነገር ረድኤት የለውም፤ወይም አይባረክም ብለው ስለሚያምኑ ነው።*

*ከየባዲ ሚካኤል የንባብ ቤት ተማሪዎች የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው፣ ተማሪዎች ገና ለልመና ሲነሡ፡-*

*ድንግል እመቤቴ ድንግል እመቤቴ፤*

*አንቺ ነሽና ምሳና እራቴ፤*

*በሰላም መልሽኝ ወደቤቴ።*

*ብለው ነው። ከዚህ አባባላቸው መረዳት እንደሚቻለው የዕለት ጉርሳቸውን የምታዘጋጅም ሆነ ከክፉ ነገር የምትጠብቃቸው <<ድንግል ማርያም>> ናት። ስለዚህ ለልመና ሲነሡ ከእሷ ጋር መሆናቸውን በልበ ሙሉነት አምነው ነው። የእሱዋን ስም ጠርተው ለምነው ሲያገኙ እነሱም የዕለት ጉርሳቸውን ያገኛሉ። ክርስቲያኖችም ሰለድንግል ማርያም ስም ብለው ስለሚሰጡ ጽድቅን ያገኛሉ።*

---

[7] ተማሪና ውሻ ምንጊዜም ባላንጦች ናቸው፡፡ በየገጠሩ ውሻ የሚመገበው የራሱ ምግብ ተዘጋጅቶለት ሳይሆን የተራረፈ ነገርን ነው የሚበላው፡፡ የቆሎ ተማሪዎችም ብዙውን ጊዜ የሚሰጣቸው ትርፍራፊ ምግብ ነው፡፡ ውሻውን ከርቀት ለመከላከል ሲባል በትሩ ረጅም መሆን ይኖርበታል፡፡ አንድ ተማሪ በልመና ላይ እያለ የቱንም ያህል ውሻ ቢያስቸግረው እራሱን መከላከል እንጂ ውሻውን መደብደብ አይችልም፡፡ ይህንን ካደረገ የሚለምነውን ሰው እንደናቀ ይቆጠርበታል፡፡ ስለዚህ የውሻውን ምግብ እንደሚወስድበት ስለሚያውቅ ሌላ እንግዳ ሲመጣ የማይጮኽ ውሻ ተማሪ ‹‹በእንተ ስማ ለማርያም›› ሲል ከሰማ ዝም ብሎ አይቀመጥም፡፡ ይህንን አጥኚው በመስክ ቆይታው ማረጋገጥ ችሏል፡፡ አጥኚው በእንግድነት ወደቤት ሲገባ ከተኛበት ያልተነሳው ውሻ ትንሽ ቆይቶ ተማሪ ለልመና ሲመጣ ከተኛበት ተነስቶ ተማሪውን ሳለማስጠጋት ትልቅ ፍትጊያ ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ ተማሪ ምንጊዜም ቢሆን ውሻ እንደሚነሳበት ስለሚያውቅ በትሩን አስቀድሞ በጥንቃቄ ይዞ ይንቀሳቀሳል፡፡

የቆሎ ተማሪ የእመቤቱን ፍቅር ለመግለጽ፣ ለልመና ወጥቶ በመንገድ ላይ እያለ ቢርበው እንኳ አኮፋዳው ውስጥ ካለ ምግብ/ፍርፋሪ አውጥቶ መብላት አይችልም፤አይፈልግም። ምክንያቱም ከአኮፋዳው ጋር አብራቸው ስትንከራተት የዋለችው <<ድንግል ማርያም>> መሸኘት አለባትና። ስለዚህ በሰላም ጎጇቸው ደርሰው ድንግል ማርያምን የመሸኘት ኃላፊነት አለባቸው። ይህ ድንግል ማርያምን የመሸኘት ሥርዓት እራሱን የቻለ ደንብ አለው። አንድ ተማሪ ዛሬ ላይ ሰላም የመለሰችው ድንግል ማርያም ነገ ሰዓቱ ደርሶ እስከምትመጣ በሰላም መሸኘት አለበት። አንድ ከልመና የመጣ ተማሪ የያዘውን አኮፋዳ እንደያዘ ወደጎጆው ዘልቆ አይገባም። ከዚህ ይልቅ በጎጆው አካባቢ ለአገኘው ለማንኛውም ተማሪ በአኮፋዳው ከያዘው የሚቀመስ ነገር <<ስለማርያም፣ የማርያም መሸኛ>> በማለት ያቀምሳል። ከዚህ በኋላ ድንግል ማርያም በሰላም ወደ ቤቱ አድርሳዋለችና ከአኮፋዳው የፈለገውን ነገር መመገብ ይችላል። ይህንን ሳያደርግ በመንገድ ከአኮፋዳው የሚበላ ነገር የቀመሰ ተማሪ ማንም ባያየውም እንኳን ሰይጣን አሳስቶኝ ነው ብሎ መጥቶ ለጓደኞቹ ይናዘዛል እንጂ ዝም ብሎ አይቀርም።

ስለሆነም ነገ ከነገ ወዲያ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እንደሚሆኑና እነሱን ከአምላካቸው ጋር የሚያገናኙ መሸጋገሪያ ድልድዮች መሆናቸውን ስለሚያምኑ የተማሪዎችን ልመና በደስታ ይቀበላሉ። የመኖር ህልውናቸውንም ይጠብቃሉ። በእነሱ አነጋገር የዛሬዎቹ ተማሪዎች ነገ <<የእግዚአብሔር ዐይኖች ስለሆኑ ለእነዚህ ተማሪዎች ሲለምኑ መስጠት እንደ ጽድቅ፣ ሳይሰጡ መቅረት ደግሞ ረድኤት እንደማጣትይቆጠራል። ተማሪዎችን የእግዚአብሔር ዐይን ብለው የሚጠሯቸውም ከዚህ ሕይወታቸው በኋላ በማንኛውም መንፈሳዊ ሕይወት ከፈጣሪያቸው ጋር የሚገናኙት በእነሱ በኩል በመሆኑ ነው። ስለዚህ የነገውን መድረሻቸውን በማሰብ ለተማሪዎች ትልቅ ክብር ይሰጣሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ተማሪ ሳይለምን ከቀረ ሰዎች ረድኤት ቀረብን፤በረከት ተለየን ብለው ያዝናሉ።[8] ለዚህ ማሳያ የሚሆነውም ተማሪዎችን ከሌሎች በልመና ከሚተዳደሩ ሰዎች ለይተው የሚመለከቱበት መንገድ ነው። ሌሎች ለማኞች ሲቆሙ <<ለማኝ የእኔ ብጤ ቆሟል>> ሲባል፣ ተማሪ ለልመና በሰው ደጅ ሲቆም ግን <<ተማሪ ቆሟል>> ነው የሚባለው። በዚህም ተማሪዎች አጥተው ወይም መሥራት ሳይችሉ ቀርተው ሳይሆን ለትምህርት ሲሉ የመረጡት

[8] ግንቦት ፳ ቀን ፳፱፣ ፳፻፫ ዓ.ም. የልምዳር አቦ ቤተ ክርስቲያን ከተማሪዎች ጋር ተገኝቼ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት አንድ አዛውንት ወደ መሪጌታውና ጥቂት ተማሪዎች ወደተቀመጡበት ጠጋ ብለው ሰላምታ ከሰጡ በኋላ ‹‹አንተ ተሜ በእኛ ጎጥ የምትለምነው አይደለህ? ›› ብለው ጠየቁ፡፡ ተማሪውም እሱ መሆኑን ሲገልጽላቸው በየኔታ ፊት የምጠይቅህ ጥያቄ ነበረኝ ብለው ወደ መሪጌታው ተጠጉ፡፡ ‹‹ዓለሜ ምን አጥፍቼ ነው መጥተህ እኔ ቤት ዘንድ ስትደርስ ሳትለምን የምታልፈው? ምን ነገር ሰማህብኝ? ክርስቲያን አደለም አሉህ? በል እስቲ ካጠፋሁም እንድክስ በየኔታና በዚህ በእንግዳው ፊት እውነቱን ንገረኝ›› ብለው በስሜት ጠየቁት፡፡ ተማሪውም በተደጋጋሚ ሲለምን ልጆቹ እየወጡ አትቁም እንደሚሉት ገልጾ፣ አዛውንቱም ልጆቹን እንደሚቆጣ ተናግረው ተለያዩ፡፡ አዛውንቱም እኔ አልዘክርም ወይ? ክርስቲያን አይደለሁምን? ለምን ክብር ይለፈኝ ብለው እንደሚቆጩ ገልጸውልኛል፡፡

የሕይወት መንገድ መሆኑን በመቀበል ይረዱዋቸዋል። አጠቃላይ በአካባቢው ስለልመናም ሆነ ስለተማሪዎች ያለው አመለካከት በጎ የሚባል ነው። ተማሪዎችን ፍጹም የረድኤትና የጽድቅ አድርገው ሲቀበሉዋቸው ማየት የተለመደ ነው።

## ፬.፬ ተሜና ትምህርቱ

በቆሎ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ቆይታ ውስጥ ሁለት ወቅቶች የዓመቱ የትምህርት ወቅቶች ተደርገው ይወስዳሉ። በእነዚህ ወቅቶች ተማሪ ከጉባኤ ወጥቶ ወደ ሌላ ቦታ አይንቀሳቀስም። በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ ዋና የትምህርት ወቅት ተደርጎ የሚወሰደው ግን የክረምት ወቅት ነው። ከዓመቱ አራት ወቅቶች መካከል ክረምት ተማሪዎች ሐሳባቸውን ሁሉ ሰብስበው ለትምህርት ራሳቸውን የሚያዘጋጁበት ጊዜ ነው።ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው፣[9] ክረምት ለትምህርት ዋና ወቅት ተደርጎ የተመረጠበት ምክንያት ከተፈጥሮ ክስተት ጋር የተያያዘ ነው። ከእነዚህ ሁሉ ወቅቶች በተለየ በክረምት ደመና በሰማይ ላይ የሚያንዣብበት፣ ጉም ምድሪቱን የሚጋርድበት፣ መብረቅና ነጎድጓድ ፍጥረትን የሚያሸብርበት ፣ ዝናብ ያለማቋረጥ የሚዘንብበት፣ ወንዞች ሞልተው ከልካቸው በላይ የሚፈሱበት፣ ወዘተ. ጊዜ ነው። ይህ ወቅት አዲስ ነገር ለመፍጠር ደግሞ የተፈጥሮ ክስተቶችን እንደግብዓት መጠቀም የተለመደ ነው። ክረምት ከሌሎች ወቅቶች በተለየ መልኩ ብዙ ነገሮች የሚከሰቱበትና የሚለዋወጡበት ጊዜ ነው። የነገሮቹ መለዋወጥና በነበሩበት አለመቆየት ለዜማና ለቅኔ ተማሪዎች የፈጠራ ልምምድ ትልቅ ድርሻ አለው። በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ የንባብ ቤትን ያለፈ ተማሪ የአስተሳሰብ ነጻነት ተሰጥቶት በራሱ አዲስ ፈጠራ እየታገዘ ትምህርቱን ይቀጥላል።

የዜማ ተማሪ ዜማውን ከነፋሱ ሽውታ፣ ከወንዞቹ ሙላት ፣ ከዛፎቹ ሽውሽውታ ፣ ወዘተ. እየቀዳ ያዜማል፤ ይለማመዳል። የቅኔ ተማሪም ዐይኑን እስከሚታክተው ከሚመለከተው ተፈጥሮአዊ ክስተት በመነሣት አዲስ ቅኔ ይፈጥራል። በአጠቃላይ የክረምቱ ወቅት ይዞት በሚመጣው ክስተት ምክንያት ለፈጠራ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ስለሆነም በዚህ ወቅት ተማሪ ከቦታ ቦታ አይንቀሳቀስም። ከጉባኤ ወጥቶ ወደ ሌላ ጉባኤ አይዞርም። ከዚህ ይልቅ በሙሉ ትኩረቱን ለትምህርቱ ብቻ ያውላል። እነዚህ ሁሉ ክስተቶች ተማሪዎች ከቦታ ቦታ እንዲዟዟሩ ወይም መምህር እንዲያማርጡ አያስችሏቸውም። ስለሆነም በዚህ ወቅት በጋ ላይ ለክረምት ብለው ያዘጋጁትን ድርቆሽ በመያዝ ባሉበት ጉባኤ ይቆያሉ። ይሄ ግን እንደየጉባኤ ቤቱ ሊለያይ ይችላል። ሌላውና ሁለተኛው ወቅት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት

[9] መረጃ ሰጪ፥-ተማሪ ጥዑመልሳን እሸቱ እና ተማሪ መንክር ግርማ (ቃለ መጠይቅ ግንቦት ፳፣ ፳፻፫ ዓ.ም. እና ሰኔ ፲፰፣ ፳፻፫)።

ተከታዮች ዘንድ <<ዐቢይ ጾም>> ተብሎ የሚታወቀው ጊዜ ነው። ይህ የጾም ወቅት ሁለት ወር የሚወስድ የጾም ጊዜ ነው። በዚህ ወቅት ጉባኤዎች ከሌላው ጊዜ በተለየ መልኩ በተማሪዎች ይሞላሉ። እንደዋና የትምህርት ወቅትም በጉጉት ይጠበቃል። ለዚህም ሁለት ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። የመጀመሪያው ተማሪዎች በጾምና በጸሎት እየታገዙ ሐሳባቸውን ሰብስበው ሲማሩ ትምህርት እንደሚሰምርላቸው በማመናቸው ነው። ሌላው ምክንያት በዐቢይ ጾም ጊዜ በሃይማኖቱ ተከታዮች ዘንድ ምንም ዓይነት ተዝካርና ሰርግ አለመዘጋጀቱ ነው። ይህ አለመደረጉ ደግሞ ተማሪዎች ድግስ ፍለጋ ከቦታ ቦታ እንዳይዞሩና ሐሳባቸውን እንዳይበትኑ፣ ከዚህ በተጨማሪ በጾም ወቅት መምህሮች ብዙ ቦታ ስለማይሄዱ ተማሪዎች እንደልብ አግኝተው የሚፈልጉትን መማር ይችላሉ።

በቆሎ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ቆይታ መረዳዳትና መተጋገዝ የተለመዱ ተግባሮች ናቸው። በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ ሁሉም ነገር የጋራ ነው። የግል የሚባል ንብረት የለም። ምንም እንኳን እያንዳንዱ ተማሪ የራሱ ጎጆ ቢኖረውም የሚኖሩት፣ የሚመገቡትና የሚለምኑት በጋራ ነው። ከዚህ ባለፈም እርስ በእርስ መከባበር፣ ለራስ ሳይሆን ለሌላ ቅድሚያ መስጠት በጉልህ የሚታዩ ባሕሪያት ናቸው። ከነዚህም መካከል ለአዲስ ተማሪ የሚደረግ አቀባበልና ለአካል ጉዳተኞች የሚደረግ እንክብካቤ ተጠቃሾች ናቸው። ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ከአንድ ጉባኤ ወደሌላ ጉባኤ ይዘዋወራሉ። ይህም በትምህርት ቤት ቆይታቸው አንዱ መገለጫቸው ነው።

ማንኛውም ተማሪ ወደ ጉባኤው ገብቶ ለመቀላቀል የሚያልፍባቸው መንገዶች አሉ። ወደ አዲስ ትምህርት ቤት የመጣ ተማሪ በመጀመሪያ ተማሪዎች በሚያዘወትሩበት አካባቢ በተለይም ቅኔ በሚቆጥሩበትና ዜማ በሚለማመዱበት አካባቢ ይቀመጥና ተማሪዎችን ይመለከታል። ይህም እንደ ጉባኤ ቤቱ የእንግዳ አቀባበሉ አንድ ወጥ አይደለም። ለተማሪዎች ጎንበስ ብሎ ሰላምታ ይሰጥና ለትምህርት መምጣቱን ይገልጽላቸዋል። እያይዞም ከመምህሩ ጋር እንዲያገናኙት ይማጸናቸዋል። ተማሪዎችም ይሁንታቸውን ገልጸው ከቆጠራ መልስ ወይም ከዜማ ልምምድ መልስ ወደጎጇቸው ይዘውት ይሄዱና ከመካከላቸው አንዱ ተመርጦ አዲስ ተማሪ እንደመጣ ለመምህሩ ይገልጻል። መምህሩም <<እስኪ ወዲህ ና በሉት>> ብለው አስጠርተው የተለያዩ ጥያቄዎችን ይጠይቁታል።



*ፎቶግራፍ ፱፡- አዲስ የመጣ ተማሪ መምህሩ እንዲቀበሉት ሲጠይቅ*

*ነገር ግን ለጥያቄ ተጠራ ማለት በጉባኤው ተቀባይነት አገኘ ማለት ላይሆን ይችላል። ይህ የሚወሰነው መምህሩ ከሚጠይቁት ጥያቄዎች በኋላ ነው። ተማሪውም በመምህሩ መጠራቱ ሲነገረው የለበሰውን <<ትዕምርተ መስቀል>> አጣፍቶ ለብሶ መምህሩን እጅ በመንሣት ፊት ለፊት ይቆማል። መምህ ሩም ከየት ሀገር እንደመጣ፣ የት የት እንደተማረ፣ ምን ሲማር እንደነበር፣ አንዱን የትምህርት ደረጃ ጨርሶ ወይስ የመምህር ለውጥ ፈልጎ መሆኑን ይጠይቁታል። ተማሪው አንድ የትምህርት ደረጃ ጨርሶ ወደሌላ ትምህርት ቤት መምጣቱን ከገለጸ ብዙም ችግር አይገጥመውም። ነገር ግን ባለበት የትምህርት ደረጃ የጉባኤ ለውጥ ከሆነ ያደረገው የመጣበትን ጉባኤ በምን እንደለቀቀ መስቀለኛ ጥያቄ ይጠየቃል። ያለፈውን ጉባኤ ለምን መቀየር እንደፈለገ አሳማኝ ምክንያት ካልተናገረ መምህሩ ላይቀበሉት ይችላሉ። ነገር ግን በመምህሩ ይሁንታን ከአገኘ ከተማሪዎች አንዱን ጠርተው <<ወስዳችሁ እግሩን እጠቡት>> ብለው ያዛሉ። በዚህ ጊዜ አዲስ ተማሪን መቀበል እንደረድኤት ስለሚቆጠር ሁሉም ተማሪዎች እነሱ ጋር እንዲያርፍ ፍላጎት ያሳያሉ። ብዙውን ጊዜ ግን መጀመሪያ ከሜዳ ያመጡት ተማሪዎች ይቀበሉትና ወደ ጎጇቸው ይዘውት ይገባሉ።*

*በተማሪዎች መንደር አዲስ ተማሪ የመጣበት ቀን ትልቅ የድግስና የመቀራረቢያ ቀን ነው። ሌሎች ተማሪዎችም ያላቸውን ነገር ይዘው ወዳረፈበት ጎጆ ይሄዳሉ። በዕለቱ ጨዋታና ቀልድ ደርቶ ያመሻል፤ ሁሉም ከእንግዳው ተማሪ ጋር አብረው ያመሻሉ። አዲሱ ተማሪም የእንግዳነት ስሜት እንዳይሰማውም ገጠመኝ ካለው*

እንዲያወራ አልያም እነሱ እያወሩ እንዲጫወት ያበረታቱታል። ከዚህ ሁሉ በኋላ የተማሪውን እግር አጥበው መተኛቸውን ለቀው ይሳድሩታል። እንግዳው ተማሪ በዕድሜ ከተቀበለው ተማሪ ያነሰም እንኳን ቢሆን እግሬን ማጠብ አትችልም ብሎ ቢግደረደር እንኳን ፈጽሞ መከልከል አይችልም። ይህ በተማሪዎች ዘንድ ደንብ (ትውፊት) ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀመዛሙርቱን እግር ዝቅ ብሎ እንዳጠበው ሁሉ ተማሪዎችም የአዲስ ተማሪዎችን እግር ሲያጥቡ የክብር ስሜት ይሰማቸዋል። ለማጠብ በመመረጣቸውም ራሳቸውን እንደ ዕድለኛ ይቆጥራሉ።



ፎቶግራፍ ፫፡- ማየት የተሳነው ተማሪ በማታ ጉባኤ ላይ እንክብካቤ ሲደረግለት

ሌላው ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚደረግ እንክብካቤ ነው። በቆሎ ትምህርት ቤቶች በሰው ሠራሽም ሆነ በተፈጥሮ አደጋ አካል ጉዳተኛ የሆኑ ተማሪዎች በብዛት ይገኛሉ። ተማሪዎች ከገጠር ቤተሰብ የሚመጡ ስለሆኑ የአካል ጉዳተኛ ከሆኑ ደግሞ ጋራ ወጥቶ ቁልቁለት ወርዶ አርሶ መኖር ስለሚያስቸግር ተምሮ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆኖ ለመኖር ሲሉ በብዛት ወደ ተማሪነት ይሰማራሉ። የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እንደሌሎች ተማሪዎች የተሻለ መምህር ፍለጋ ከአገር አገር አይዘዋወሩም።

እነዚህ ተማሪዎችም አንድ ጊዜ በአረፉበት ጉባኤ ብዙ ስለሚቆዩና በጉባኤው በደንብ ስለሚታወቁ ብዙ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል። በጉባኤ ላይ ሲገኙ፣ በልመና ጊዜና በቤት ውስጥ ሁሉ ልዩ እንክብካቤ አይለያቸውም። የአካል ጉዳተኝነታቸው መጠን ከባድ ከሆነ፣ ሌሎች ተማሪዎች በቆዩበት ጊዜ ሁሉ ምግብ ለምነው በማምጣትና ውኃ ከወንዝ በመቅዳት ያኖሯቸዋል። በአንጻሩ የአካል ጉዳተኝነታቸው መጠን ቀለል ያለ ከሆነና <<በእንተ ስማ ለማርያም>> ብለው ለምነው መኖር እንደሚችሉ ካሳወቁ፣ ቅርብ ያሉ መንደሮች ያለ ዕጣ ይሰጣቸዋል። እነሱም ራሳቸውን በራሳቸው ያስተዳድራሉ። የጥገኝነት ስሜት እንዳይሰማቸውም በጋራ ርብርብ ጎጆ ይቀለስላቸዋል።

## ፬.፰ ተሜና የፈጠራ ክሂሎቱ

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የቅኔና የዜማ ተማሪዎች የተጻፈ ነገርን በማንበብ ወይም በመድገም ከመወሰን አልፈው የራሳቸውን የመፍጠር ችሎታ ተጠቅመው አዲስ ነገር ይፈጥራሉ። የሐሳብ ነጻነትም ይሰጣቸዋል። አዲስ ነገር ለመፍጠርም ብዙ ጊዜ በተመሥጦ ውስጥ ይሆናሉ። ለዚህ ደግሞ የሚመርጡት ቦታ ከአካባቢው ርቆ በመሄድና ሰው የማይበዛበትን ቦታ በመምረጥ ወደ ጫካ ይገባሉ፤ ብቻቸውን በመሆንም ወደ ውስጣቸው ይመለከታሉ። አዲስ ነገር ለመፍጠርም ሲወድቁና ሲነሡ ማየት የተለመደ ነው። ዛፍ ላይ ይወጣሉ፤ ወደ ሰማይ ያንጋጥጣሉ፣ ተሸፋፍነው ይተኛሉ፤ አንገታቸውን በጉልበታቸው ቀብረው ይቀመጣሉ። በአጠቃላይ እያንዳንዱ ተማሪ ለብቻው በመሆን በሐሳብ ከአካባቢው ግርግር በመራቅ ወደ ውስጡ ለመመልከት ጥረት መታየቱ የተለመደ ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ በየቀኑ የሚደረግ ክስተት እንጂ የአንድ ጊዜ አጋጣሚ ብቻ አይደለም። የቅኔ ተማሪ በጠዋት ታሪክ ይነገረዋል፤ የተነገረውን ታሪክ መሠረት አድርጎም ቅኔ ቆጥሮ እንዲመጣ የቤት ሥራ ይሰጠዋል። የፈጠረውን ቅኔም ለመምህሩ ነግሮ ማሳረም ይኖርበታል። ስለዚህ ይህንን ቅኔ ለመፍጠር ለብቻው በመሆን ሲያወራ፣እጁን ሲያወናጭፍ ወይም አንድ ቦታ ላይ ዐይኑን ተክሎ በሐሳብ ተውጦ ማየት የተለመደ ክስተት ነው። ምክንያቱም የተነገረውን ታሪክ ከሁኔታው ጋር አዛምዶ የራሱን ቅኔ መፍጠር ይጠበቅበታልና። የዜማ ተማሪም እንዲሁ ከአካባቢው ራቅ ወዳለ ቦታ በመሄድ ሲጮህ፣ ሲያንጎራጉር፣ የሚያለቅስ ሲመስል በአጠቃላይ ድምፁን ለመግራትና ዜማውን በሚገባ ለማማሳመር ያለማቋረጥ ብቻውን በመሆን ሲለማመድ ይታያል። አልገራ ያለ ድምፁን የሚገራው፣ የዜማ አወራረዱን ልክ የሚያመጣው ብቻውን በመሆንና ያለማቋረጥ በመለማመድ ነው።

በቆሎ ተማሪዎች ሕይወት ውስጥ ተማሪዎች የትምህርት ደረጃቸው ከፍ እያለ ሲሄድ በሚማሩበት ጉባኤም ሆነ በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚያገኙት ክብር አብሮ ይጨምራል። በቅኔ ጉባኤ ውስጥ የተሻለ ዕውቀት ያለው ተማሪ ‹የኔታ› ተብሎ በመምህራኑ ስም መጠራት ይጀምራል። ይህ ከተማሪነት ስም ወጥቶ የኔታ መባሉ ትልቅ የደረጃ ለውጥ ነው። ዕድሜያቸው ምንም ይሁን ምን በጉባኤው ዘንድ በሚያሳዩት ዕውቀት ሁሉም ነገር ለእነሱ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።መምህሮቹን ተክተውም ጉባኤውን ያስተምራሉ፤ አንተ መባል ይቀርና <<አንቱ>> ይባላሉ። ከእውቀታቸው ጋር ተያይዞ የሚመጡ ብዙ ማዕረጎችንም ያገኛሉ[10]። ከዚህ ባለፈ በእውቀታቸው መሠረት ከመምህሮቻቸው ጋር ይቀመጣሉ፣ የቅርብ አማካይ ይሆናሉ። በተለያዩ ግብዣዎች ላይም በልመና ሳይሆን ከመምህራቸው ጋር በክብር ይገኛሉ። የተማሪነት ሕይወትን እየተዉ ወደ መምህርነት ይሸጋገራሉ። በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ ዕውቀትና በጉባኤው ውስጥ የሚሰጥ ክብርና ማዕረግ ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው። ከዚህ በኋላ እነዚህ ተማሪዎች ከሚማሩበት ጉባኤ አልፈው በማኅበረሰቡ ዘንድ <<የየኔታ እገሌ ተከታይ>> እየተባሉ የሚሰጣቸው ደረጃም ይጨምራል።



ፎቶግራፍ ፭፡- በዕውቀት የተሻለው ተማሪ በመምህሩ ቦታ ተተክቶ ተማሪዎችን ዜማ ሲያስቀጽል

10 በዕውቀታቸው መሠረት ከመምህሮቻቸው ጋር ይቀመጣሉ፡፡ የቅርብ አማካሪ ይሆናሉ፡፡ በተለያዩ ግብዣዎች ላይም በልመና ሳይሆን ከመምህራቸው ጋር በክብር ይገኛሉ፡፡ የተማሪነት ሕይወትን እየተዉ ወደ መምህርነት ይሸጋገራሉ፡፡ በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ ዕውቀትና በጉባኤው ውስጥ የሚሰጥ ክብርና ማዕረግ ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው፡፡ ከዚህ በኂላ እነዚህ ተማሪዎች ከሚማሩበት ጉባኤ አልፈው በማኅበረሰቡ ዘንድ ‹‹የየኔታ እገሌ ተከታይ›› እየተባሉ የሚሰጣቸው ደረጃም ይጨምራል፡፡ ከዕውቀታቸው ጋር በተያያዘ በማኅበረሰቡ የሚጣልባቸው ግዴታም እንዲሁ ይኖራል፡፡ ስለሆነም የማኅበረሰቡን ወግና ባህል ማወቅና መጠበቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለያዩ ጥሪዎች (ግብዣዎች) ጊዜም ምንም ዓይነት ስሕተት መሥራት አይጠበቅባቸውም፡፡ ጠጥቶ መስከር ወዘተ. የመሳሰሉት ነገሮች በማኅበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ቦታ ያጎድፉባቸዋልና፡፡

በእያንዳንዱ የቆሎ ትምህርት ቤት ጉባኤ ውስጥ የሚገኘው አንድ መምህር ብቻ ነው። አንድ መምህር ብቻ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ብዙውን ጊዜ በዕውቀቱ የተሻለ ተማሪ እየተመረጠ የመምህሩን ቃል/ትምህርት በመቀበል ለተማሪዎች ያስተላልፋል። መምህሩ በዓቅም ደከም ያሉ ከሆኑም ተማሪውን እንደ ድምፅ ማጉያ በመጠቀም ይገለገሉበታል። የተመረጠው ተማሪም ያለመሰልቸት ከመምህሩ እየተቀበለ በከፍተኛ ጩኸት ለተማሪዎች ይነግራል። ከዚህ ችግር በመነሣት አንድ ተማሪ ሲማር ማለትም ዳዊት ሲደግም፣ ዜማ ሲያወርድ ወይም ቅኔ ሲነግርና ሲዘርፍ ሌሎች ቁጭ ብለው የመከታተል ግዴታ ይጣልባቸዋል። ይህንን የሚያደርጉት በእያንዳንዱ ጉባኤ ላይ ጀማሪዎችም ሆኑ ነባር ተማሪዎች በጋራ በመሆን ነው።



ፎቶግራፍ ፩፡- ነባር ተማሪዎች ቅኔ ሲነግሩ ጀማሪ ተማሪዎች ቁጭ ብለው ሲመለከቱ

አንድ ተማሪ ሲሳሳት ያለምንም መደበቅና መሸፋፈን የትኛወም ተማሪ ተነሥቶ እርማት ይሰጣል። በዚህም እርስ በርሳቸው ዕውቀታቸውን ሳይደብቁ ይማማራሉ።

## መደምደሚያ

ይህንን ጥናት ለማድረግ ያነሣሣኝ ዋነኛ ምክንያት፣ የቆሎ ተማሪና ሕይወቱ፣ የትምህርት ሥርዓቱና ፈጠራዊ ስልቱ ለቤተ ክርስቲያናም ይሁን ለአገሪቱ ያደረገው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ሆኖ ሳለ በተመራማሪዎች ዘንድ የሚገባውን ያህል ትኩረት አለማግኘቱ ነው። እንዲሁም የሚጠቀሰው የቆሎ ተማሪዎችን ሕይወት በሰፊው የዳሰሰ ጥናት አለማግኘቴ ነው። ከዚህ በተጨማሪም በአደግሁበት ፍኖተ ሰላም አካባቢ ለቆሎ ተማሪዎች ቅርበት ስለነበረኝ በትምህርት ቤት ሕይወታቸው ተደጋግመው ከሚከሰቱ ሁኔታዎች በመነሣት ሕይወታቸው ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ያለኝ ጉጉት ነው። ጥናቱ ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሣው የቆሎ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ሕይወት ምን እንደሚመስል ለማሳየት ነው። ይህ ዓላማ ግቡን ይመታ ዘንድ ለጥናቱ ግብዓት የሆኑ መረጃዎች ከቀዳማይና ካልዓይ ምንጮች በምልከታና በቃለ መጠይቅ ተሰብስበዋል።

በዚህ ጥናት በቆሎ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ቆይታ ጊዜ ተደጋግመው የሚከሰቱና የተማሪዎች መገለጫ የሆኑ እንደ ጉዞ፣ ስም ቅየራ፣ ልመና፣ መረዳዳት፣ ትምህርትና ወቅት፣ ዕውቀትና ማኅበራዊ ደረጃ እንዲሁም እርስ በርስ መማማር የመሳሰሉ ጉዳዮች ተዳስሰው ቀርበዋል። ከጥናቱ ውጤት ማየት እንደተቻለው፣ ተማሪዎች የሚፈጽሟቸው እንደ ጉዞ፣ ስም ቅየራ፣ ልመና ያሉ ጉዳዮች በተማሪዎች ዘንድ ሃይማኖታዊ፣ ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊ ምክንያቶችን የያዙ ናቸው። እንዲሁም ማኅበረሰቡ ለተማሪዎችና ለልመና ከበሬታና በጎ ዕይታ የተማሪዎቹን ሞራል ከመገንባት አልፎ በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ቁሳዊ ድጋፍ እንዳይለያቸው አድርጎአል። የጥናቱ ግኝት እንደሚያሳየው፣ የክረምት ወቅትና የዐቢይ ጾም ለተማሪዎች ሥነ ልቡናዊ መረጋጋትና የፈጠራ ክሂሎት ተስማሚ ጊዜያት ናቸው። እነዚህ ጊዜያት ተማሪዎቹ ሐሳባቸውን ሰብስበው ለመማርና አዲስ ነገር ለመፍጠር ስለሚያግዟቸው በጉጉት የሚጠበቁ የትምህርት ወቅቶች ናቸው።

ሌላው በጥናቱ የታየው ጉዳይ፣ ተማሪዎች የሚፈጽሟቸው እንደጉዞ፣ ስም ቅየራ፣ ልመና ያሉ ጉዳዮች በተማሪዎች ዘንድ ሃይማኖታዊ፣ ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊ ምክንያቶችን የያዙ ሆነው መገኘታቸው ነው። ክርስቲያኖች እነዚህ የቆሎ ተማሪዎች ነገና ከነገ ወዲያ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እንደሚሆኑና እነሱን ከአምላካቸው ጋር የሚያገናኙ መሸጋገሪያ ድልድዮች መሆናቸውን ስለሚያምኑ የተማሪዎችን ልመና በደስታ ይቀበላሉ። የመኖር ህልውናቸውንም ይጠብቃሉ። በእነሱ አነጋገር የዛሬዎቹ ተማሪዎች ነገ —የእግዚአብሔር ዐይኖች“ ስለሆኑ ለእነዚህ ተማሪዎች ሲለምኑ መስጠት እንደጽድቅ፣ ሳይሰጡ መቅረት ደግሞ ረድኤት እንደማጣት ይቆጠራል።

ተማሪዎችን የእግዚአብሔር ዐይን ብለው የሚጠሯቸውም ከዚህ ሕይወታቸው በኋላ በማንኛውም መንፈሳዊ ሕይወት ከፈጣሪያቸው ጋር የሚገናኙት በእነሱ በኩል መሆኑን በመረዳታቸው ነው። ስለዚህ የነገውን መድረሻቸውን በማሰብ ለተማሪዎች ልመና ትልቅ ክብር ይሰጣሉ። እንዲያውም የቆሎ ተማሪ ወደ ደጃቸው ደርሶ ሳይለምን ከቀረ ረድኤት ቀረብን፤ በረከት ተለየን ብለው እንደሚያዝኑ በጥናቱ ተመልክቶአል።

ሌላው በጥናቱ የታየው ጉዳይ ትውፊታዊ (ፎክሎራዊ) እምነት ነው። የቆሎ ተማሪ የእመቤቱን፣ የድንግል ማርያምን፣ ፍቅር ለመግለጽ፣ ለልመና ወጥቶ በመንገድ ላይ እያለ ቢርበው እንኳን አኮፋዳው ውስጥ ካለ ምግብ/ፍርፋሪ አውጥቶ መብላት አይችልም፤አይፈልግምም። ምክንያቱም ከአኮፋዳው ጋር አብራቸው ስትንከራተት የዋለችው ድንግል ማርያም መሸኘት አለባትና ነው። ስለዚህ በሰላም ጎጇቸው ደርሰው ድንግል ማርያምን የመሸኘት ኃላፊነት አለባቸው። ይህ ድንግል ማርያምን የመሸኘት ሥርዓት ራሱን የቻለ ደንብ አለው። አንድ ከልመና የመጣ ተማሪ የያዘውን አኮፋዳ እንደያዘ ወደ ጎጆው ዘልቆ አይገባም። ከዚያ ይልቅ በጎጆው አካባቢ ለአገኘው ለማንኛውም ተማሪ በአኮፋዳው ከያዘው የሚቀመስ ነገር <<ስለማርያም የማርያም መሸኛ>> በማለት ያቀምሳል። ከዚህ በኋላ ድንግል ማርያም በሰላም ወደ ቤቱ አድርሳዋለችና ከአኮፋዳው የፈለገውን ነገር አውጥቶ መመገብ ይችላል። ይህንን ሳያደርግ በመንገድ ከአኮፋዳው አውጥቶ የቀመሰ ተማሪ ማንም ባያየውም እንኳን ሰይጣን አሳስቶኝ ነው ብሎ መጥቶ ለጓደኞቹ ይናዘዛል እንጂ ዝም ብሎ አይቀርም።

# ማጠቀሻ ጽሑፎች


ሀብተማርያም ወርቅነህ:: (፲፱፻፷፫):: *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት*:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት::

ቴዎድሮስ ገብሬ:: (፳፻፩):: በይነ ዲስፕሊኒያዊ የሥነጽሑፍ ንባብ:። አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ::

ኪዳነማርያም ጌታሁን: : (፲፱፻፹):: *ጥንታዊ የቆሎ ተማሪ::* አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት::

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር: :(፳፻):: *መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት* :: አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር::

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ጥናትና ምርምር ማእከል: (፲፱፻፺፪):: *አማርኛ መዝገበ ቃላት፤* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ::

ዳንኤል ክብረት። (፳፻፯)። *አራቱ ኃያላን ። አዲስ አበባ፤ አግዮስ ኅትመትና ጠቅላላ ንግድ ሥራ ኃላ.የተ. የግል ማኅበር::*

ፈቃደ አዘዘ። (፲፱፻፺፩):: *የሥነ-ቃል መምሪያ::* አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት::

Alemayehu Moges. (1971). *The Traditional Church Education.* Addis Ababa, Hile Selassie University.

Ben Amos, Dan. (1971). ``Towards a Definition of Folklore in Context.`` Journal of American Folklore, vol. 84, No.331,pp.315.

Dorson, M. Richard. (Ed), (1972). *Folk and Folk Life.* USA: The University of Chicago Press LTD.

Ephraim Isaac (Professor), (2010). ``Social Structure of the Ethiopian Church, in Ethiopia.``

Observer: Journal of Independent Opinion, Economics, History and the Arts, Vol. XIV,

No.4, 243; Lule Melaku, History of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church: Part Two and Three, 2010, 70.

Finnegan, Ruth. (1972). *Oral Tradition and the Verbal Arts: A Guide to Research Practices*. London, Routledge.

Goldstein, Knneths. (1964). *A Guide for Field Workers in Folklore.* Pennsylvania, Folklore Associates inc.

Martha C. Sims and Martine Stephens. (2005). *Living Folklore: An Introduction to the study of people and their Tradition.* Ohio: Utah State University Press.

Georges, Robert A. and Jones, Michael Owen. (1995). *Folkloristies: An introduction*. USA: Indiana University Press.

Moberg, David O. (1972). *The Church as a social Institution.* USA: Prentice-Hall Inc.

Oring, Elliot. (1994). ``The interests of Identity. `` The Journal of American Folklore. Vol.107, No.424, pp.242-247, University of Illinois press.

Pankhurst, Richard. (Ed). (1966). *Ethiopia: Church, State, and Education in Africa.* Scanlon David G. New York: Teachers College Press, 1966.